## ኩልኳሎዎች - המשך פעילויות בעקבות הסיפור




በ: ዳቲያ ቤን-ዶር
ምሳሌዎች: ኦራ አየለት
הוֹצָאָה: מודן
የእድሜ ክልል: ጨቅላ ህፃናት

קְרִיאָה

**ለቤተሰባዊ ንባብ የሚሆኑ ጠቃሚ ምክሮች**

ከትንሽነታቸው ጀምሮ መጻሕፍትን ማንበብ ለታዳጊ ሕፃናት እድገት አስተዋጽኦ ያደርጋል፡- ለለጋ ህጻን በሚስማማ መንገድ በዝግታና በቀስታ እንዲጀምሩ እንመክርዎታለን፡- ለመጀመር አንዳንዶች መጽሐፉን መንካካትን፣ መዝጋትንና መክፈትን አልፎ ተርፎም 'መቅመስን' ሊመርጡ ይችላሉ። አንድ ገጽ በማንበብ መጀመር ይችላሉ። እርሡን !ይለማመዱ፣ ገጾችን ይጨምሩ። ይሄው – መጽሐፉ ጓደኛ ሆነ ማለት ነው

ዳትያ ቤን-ዶር (1944) በአንድ ከመንፈቅ ዓመቷ ከግብፅ ወደ እሥራኤል ዓሊያ አድርጋለች። በሙያዊ ሥራዋ መጀመሪያ ላይ በሙዚቃ ትምህርት በመሠማራት ሠርታለች። ለቅድመ ትምህርት ቤት ልጆች ለብዙ የቴሌቭዥን ፕሮግራሞች ስክሪፕቶችንና ዘፈኖችን ጽፋለች፡- "ቆንጆ ቢራቢሮ"፣ "የሰሊጥ ጎዳና" እና ሌሎችም። የመዋዕለ ሕፃናት ዜማዎቿና የህፃናት መጽሃፎቿ የታወቁና የተወደዱ ሲሆኑ ከነዚህም መካከል፡- "እኔ ሁልጊዜ እኔው እንደሆንኩ እቀራለሁ"፣ "የዋዘኞች ፊደላት" እና "የሞኞች መጽሐፍ"። ቤን-ዶር በልጆች ሥነ ጽሑፍ ላይ ላደረገችው አስተዋፅዖ ብዙ ሽልማቶችን አግኝታለች።

קְרִיאָה

### በምሥሎች መገንዘብ

በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ምሥሎች መመልከት ለህፃናት የቋንቋ እድገት አስተዋጽኦ ያደርጋል። ምሥሉን አንድ ላይ ማየቱና መግለጹ ተገቢ ነው፡- ለምሣሌ፡- “ይሄ ፊኛ ነው፣ ፊኛ ክብ ነው፣ ፊኛው ወደ ላይ እየበረረ ነው”። በዚህም የሕፃናቱን የቃላት አነጋገር ያበለጽጋሉ።

שִׁלּוּב הַסֵּפֶר

### ለሁሉም ቤተሰብ የሚሆን እንቅስቃሴ

እያንዳንዱ ግጥም ለሁለት ተግባር የሚሆን ሀሳብ ስላለው ለተጨማሪ የቤተሰብ አባላት ወይም ጓደኞች እንዲስማማ ማድረግ ይችላሉ። ለምሣሌ:- “ሁለት ጊዜ መሳም” በሚለው ግጥም ውስጥ በቤት ውስጥ ያለውን ሁሉ ሁለት ጊዜ መሳምና ማቀፍ ይችላሉ። “አይጥ” በሚለው ግጥም ውስጥ ጥቁሩን ድመት መሆን ይችላሉ – ጣቶችዎን ወደ ‘ጆሮ’ ያጣጥፉና “ሩጥ ሩጥ ሩጥ ... እና ... ሆፕ! ወደ ጉድጓዱ ግባ” ብለው ሲጣሩ ሁሉም ሰው እየሮጠ ይሸሸጋል። ውስጥ

שִׂיחָה

### ከመጽሃፉ ወደ ሕይዎት

ግጥሞችን ወይም ሀረጎችን ከመጽሃፍቱ ወደ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎ ማካተት ይችላሉ። ለምሣሌ:- ታዳጊዎች አንድን ነገር እምቢ ሲሉ:- “ዔሊው እንደማይፈልግ አንተ/ቺም አትፈልግ/ጊም?” ወይም አንድ ላይ ቢራቢሮ በመመልከት “አንድ ቆንጆ ቢራቢሮ ወደ እኔ መጥቶ በእጄ በረረ” የሚለውን ግጥም ማለት ይችላሉ።

עוד פעילויות באתר ספריית פיג'מה www.pjisrael.org